# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

5



ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# የዘመቻው ድል–የአብዮታውያን ድል

በየካቲት ወር ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ታሪካዊ የነፃነት ተጋድሎ አገሪቱን በአብዮታዊ ማዕበል ማጥለቅለቅ ከጀመረበት ወቅት አንሥቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ አኩሪና አዳዲስ የታሪክ ገጾች በትግል በመጻፍ ላይ ይገኛል ። ምንም እንኳን ከየካቲት ወዲህ የተገኙት ታላላቅ ድሎች ከፍተኛ መስዋዕትነትን የጠየቁ ቢሆኑና ለወደፊቱም ገና ብዙ ትግል ቢጠብቀንም የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ወደነፃነታቸው በሚያደርጉት የትግል ጉዞ ከመቼውም ይበልጥ ገፍተውና ወደግባቸው ተቃርበው እናገኛቸዋለን ።

የካቲት ፷፮ የከፈተው አዲስ የትግል ዘመን እንዲጠባ በተደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ ወጣቱ የኢትዮጵያ ትውልድ በብዙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ንጹሕ ደም ፤ የስደት መከራ ፤ የእሥራትና የግርፋት ስቃይ የከፈለው ታላቅና አኩሪ አስተዋፅኦ አለው ። ከየካቲት ወዲህ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር እያነሣ የታገለባቸውና አስፈላጊም ሲሆን ፤ የተሰዋላቸው አብዮታዊ መፈክሮች በሀገራችን ምድር ተዘርተውና ስር ሰደው የማይበገሩ የለውጥ ኃይሎች እስኪሆኑ ድረስ በለጋ ትከሻው ተሸክሞ ከዚህ ያደረሳቸው ይህ ወጣቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ነው ።

ባለፉት አስር ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቸውም ይበልጥ የተደፈረው ብሔራዊና ሰብአዊ መብቱ ጨርሶ እንዳይደመሰስ በግንባር ቀደምትነትና በአስደናቂ ጀግንነት ሲጋፈጥና ሲከላከል የቆየው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ነው ። የፊውዳሊዝም ፤ የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ከባድ ቀንበር የተጫነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ጨርሶ እንዳይታፈን ያልተሰጣቸውን ነፃነት ከፊውዳሊስቱ አገዛዝ ተናንቀው በመቀማት የሕዝቡን ድምፅ ሲያስተጋቡ የቆዩት የተማሪ ማኅበራት ጋዜጦችና መጽሔቶች ናቸው ።

መጭው ትውልድ ያለፈውን የትግል ዘመን በአጠቃላይ እየመረመረ በሚተነትንበት ጊዜ ይህ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ወጣቶች በመራራ ትግላቸው የጻፉት ገጽ በኢትዮጵያ ጭቁኖች የረዥም የትግል ታሪክ ውስጥ አሸብርቀው ከሚታዩት ገጾች አንዱ እንደሚሆን አንጠራጠርም ።

የየካቲት አብዮታዊ ማዕበል ከፈነዳበት ወቅትም አንሥቶ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለትግላቸው ይበልጥ ጥራት ሰጥተው ከሕዝብ በመዋሐድ ታገሉ እንጂ ሕዝቡ በሚሊዮን እየተቆጠረ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ በመታገሉ ወጣቱ ትውልድ ከታታሪነቱና ከታጋይነቱ የቀነሰው ነገር የለውም ። አሁንም ቢሆን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ወጣቶች ከየካቲት ወዲህ ለተገኙት ድሎች የወሰዱት የትግል ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው ።

የኢትዮጵያ ወጣቶች በፊውዶ ፋሽሽቱ አገዛዝ ስር ይታገሉ በነበረበት ወቅት የታሪክ ሂደት ለጊዜው በግንባር ቀደምነት አሰልፎ ቢያታግላቸውም የነፃነቱ ትግል ምሰሶ ፤ የትግሉ ድል ብሶትና የታሪኩ ባለቤት ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ እንደሆነ ለማወቅ ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ። ስለሆነም በትግሉ አፍላ ውስጥ «ተማሪና ምሁር ከገበሬውና ከሠራተኛው ተዋሐድ ፤ ከነርሱም ተማር መልሰህም አስተምር የሚለው» አብዮታዊ መፈክር « ከመሬት ለአራሹ» እኩል ፤ ከዚህ አብዮታዊ የትግል አርማ ጋር አብሮ ከትግል በትግል ለትግል ተወለደ ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ከሕዝቡ ለመዋሐድ የሚያደርጉት ተጋድሎ መሬትን ለአራሹ አድርጎ የኢትዮጵያን ጭቁኖች ከፊውዳል ጨለማ ለማላቀቅ ከሚደረገው ትግል በምንም ዓይነት የማይነጠል የአብዮታዊው ትግል አካል ሆነ ።

ስለሆነም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ገፍቶ የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በታወጀ



በት ጊዜ ተራማጆች ዘመቻውን የየካቲት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ካስገኛቸው ዓቢይ ድሎች እንደአንዱ ተቆጥሮ በመሥዋዕትነት የተጐናጸፉት የትግላቸው ፍሬ ብመሆኑ አብዮታዊ ወጣቶች ዘመቻውን በታላቅ ደስታ ተቀበሉት ። ነገር ግን ዘመቻው የትግል ውጤት ብቻ አልነበረም ። በአብዮታዊ ወጣቶች እጅ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ለማንቃትና ለማደራጀት የሚረዳ የትግል መሣሪያም ነበር ።

ስለሆነም እንደማንኛውም የሕዝብ ድል ዘመቻው ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የአድኃሪ ኃይሎች ተቃውሞ ነበረበት ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ከጭቁኑ ሕዝብ እንዳይዋሐዱ አድኃሪ ኃይሎች ያላመጡት ክርክር ፤ ያልሞከሩት ሴራ ፤ ያልገለበጡት ድንጋይ አልነበረም ።

ነገር ግን ዘመቻውን ለማደናቀፍ አድኃሪዎችና ተራማጅ መሰል ኃይሎች ያመጡት መከራከሪያ አንደኛ የኢትዮጵያ አብዮት ወሳኝ የሆነው ኃይል የነቃ ፤ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል መሆኑን ፤ ሁለተኛ የአብዮታዊ ወጣቶች ከሕዝቡ መዋሐድ በዚህ በንቃትና በድርጅት ግንባር እጅግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ለማስካድ አልቻለም ። ቢሆንም ወደኋላ ላይ ዓይን እያወጡ ፤ «ዘመቻው መበተን አለበት ፤ መምሪያው መዘጋት አለበት » ብለው የሞት ሞታቸውን ቢከራከሩም ፤ አድኃሪዎችና ቡችሎቻቸው መጀመሪያ ላይ ዘመቻውን ለመበተን የሞከሩት ለኢትዮጵያ አብዮት የሚቆረቆሩ እየመሰሉ ነበር ።

«ዘማቾች ከከተማ ወደገጠር መሔዳቸው አብዮቱን ያዳክማል ፤ ደርጉ እንዲደላደል ያመቻዋል» በማለት ከነቃ ፤ ከተደራጀና ከታጠቀ የሰፊው ሕዝብ ትግል ይልቅ የኢትዮጵያን አብዮት የወደፊት ዕድል በተማሪዎች ላይ ያረፈ ለማስመሰል የተደረገ ክርክር ነበር ። የታሪክ ፈጣሪ ሰፊው ሕዝብ ነውና ይህ ክርክር አላዋጣም ። በሌላ በኩል ደግሞ በአብዮታዊ ትግል አፍላ ውስጥ ሁሉ ነገር ከሰማይ ተስተካክሎ ይወርድ ይመስል ፤ «ይኽ ይኽ አልተሟላም እስኪሟላ ድረስ አትዝመት» በማለት የኢትዮጵያ ወጣቶች ከጭቁኑ ሕዝብ ለመዋሐድ እንዳልታገሉ ፤ እንዳልሞቱና እንዳልተሠው ሁሉ ዘመቻው በወርቅ ትሪ ላይ ካልተሰጣችሁ አትቀበሉ የሚል ሌላ ክርክር ተነሳ ። ታጋይ ዘማቾች ፤ አብዮታዊ ወጣቶችና ተራማጆች ይህንን «ሱሪ ባንገት አጥልቁ» የሚለውን አድኃሪ አቋምም ተዋግተው አጋለጡት ። ከሁሉ «የረቀቀ» የአድኃሪዎችና የተራማጅ መሳይ ቀልባሾች ሌላ መከራከሪያም ነበር ። ይኽ ደግሞ አንዳንዴ ተራማጅ ጥያቄዎችን አንዳንዴም ደግሞ ተራማጅ መሳይ ቀልባሽ መፈክሮችን እያነሣ « እነዚህ ጥያቄዎች ካልተሟሉ ዘመቻው መካሔድ የለበትም » የሚል አቋም ነበር ። እዚህም ላይ ተራማጅና ታጋይ ዘማቾች አልተወናበዱም ። አሳሳች መፈክሮችን በትግል አጋለጡ ። ትክክለኛ የሆኑ መፈክሮችን ደግሞ ተቀበሏቸው ፤ አቀኛቸው ። ነገር ግን አድኃሪዎችና ተራማጅ መሳይ አወናባጆች እንደሚሏቸው በነዚህ መፈክሮች አሳበው ዘመቻውን አልተቃወሙም ። እንዲያውም የአብዮታውያን እምነት በሰፊው ሕዝብ ትግል ብቻ በመሆኑ እነዚህን መፈክሮች ይዘው ከሕዝቡ ለመዋሐድ ዘመቱ ።

ዘመቻው በቆየበት የአስራስድስት ወራት ዘመን ዘመቻውን በሚደግፉና መቀጠሉን በሚፈልጉ ገበሬዎች ፤ አብዮታዊ ወጣቶች ፤ ተራማጅ አዝማቾች በአንድ በኩል ፤ ፊውዳሎች ፤ አድኃሪ ወጣቶችና አዝማቾች በሌላ በኩል ከፍተኛና የተወሳሰበ ትንንቅ ሲያካሂዱ ቆይተዋል ። ከየካቲት ወዲህ በኢትዮጵያ የተቀያየረው የመደቦች አሰላለፍ ወጣቱንም አሰላለፉን እንዲለውጥ ስላደረገው በተለይ አብዮቱን ለመግፋት በሚፈልጉ ወጣቶችና የተራማጅ ትግል ሚናቸው ባከተመ በአብዮቱ የታለፉ ወጣቶች መሐከል እጅግ ከፍተኛ ትግል ተካሂዷል ። ፀረ—አብዮት ኃይሎች ዘመቻውን ለማስረዝ አብዮታዊ ኃይሎች ደግሞ ያለውን ችግር ሳይከዱ የመጣውን መከራ ሁሉ እየተወጡ ዘመቻው እንዲቀጥል የተፋፋመ የመደቦች ትግል በዚሁ በዘመቻው ጉዳይ ሲያካሂዱ ቆይተዋል ።

በዚህ ትግል ውስጥ አድኃሪ ኃይሎች ወጣቱ ውስጥ ሰርገው ባስገቧቸው ቡችሎቻቸው ብቻ ሳይሆን በቀጥታ በኃይልና በዓመፅ ለመጠቀም ስለቻሉ ከጭቁኑ ገበሬ ተዋህደው ያስተማሩት ፤ ያደራጁትና የነፃነቱን ፈለግ ያሳዩት ወገኖቻችን ብዙ ስቃይ ደርሶባቸዋል ። ተገርፈዋል ፤ ታስረዋል ቆስለዋል ፤ ተንገላተዋል ። ከነዚህ ተራማጅ ወገኖቻችን መሐከል አንዳንዶቹ ለጭቁኑ ወገናቸው የተሻለ ቀን ለማምጣት ፤ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያችን ጽኑ መሠረት ለመጣል ባደረጉት ቆራጥ ተጋድሎ የመጨረሻውን መሥዋዕትነት በመቀበል ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል ።

አብዮታዊ ወጣቶች የአድኃሪዎችና የተራማጅ መሰል አወናባጆችን ሰበብ አስባብም ሆነ ፀረ—አብዮትን አመፅ መቋቋም የነፃነቱ ትግል የማይነጠል አካል መሆኑን በመገንዘባቸው ከጭቁኑ ገበሬ ተዋህደው የሚያካሔዱትን አብዮታዊ ተግባር ሊፈታና ዘመቻውን ሊበትን የቻለ ኃይል አልመጣም ። እርግጥ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ተረሽነዋል ፤ እርግጥ አንዳንድ ታጋይ ዘማቾች የአወናባጆችን ተጽዕኖ መቋቋም ከአቅም በላይ እየሆነባቸው ኮብልለዋል ። እርግጥ አድኃሪ ዘማቾች የዘመቻውን ዓላማ በመቃወም ጣቢያቸውን እየጣሉ ወደየቤታቸው ተመልሰዋል ። ነገር ግን ይህ ሁሉ አንድ መሠረታዊ የሆነ ሃቅ ሊያስረሳን አይገባም ። አብዛኞቹ ዘማቾች በታሪክ ፊት በአብዮቱ ፊትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት የተቀበሉትን ኃላፊነት ከግቡ ለማድረስ እስከመጨረሻ ታግለዋል ። በአብዮቱ አምነው ፤ በዘመቻው አምነው ከየትም አቅጣጫ የሚሰነዘረውን ፀረ—ሕዝብ ተጽዕኖ ተቋቁመው ጭቁኑን ገበሬ አንቅተዋል ። አደራጅተዋል ።

በትግል የአድኃሪዎችንና የአወናባጆችን ሴራ አክሽፎ ዘመቻው የመጀመሪያውን ዙር በማጠናቀቁ ብቻ የኢትዮጵያ ወጣቶች ታሪካዊ ተልእኮ ተፈጸመ ማለት አይደለም ። በዘመቻ ላይ በቆዩበት የትግል ወቅት እነሱም ከአብዮቱ ብዙ ተምረዋል ። አብዮት ረዥም የተወሳሰበና ብዙ መውደቅ መነሳት የሚያጠቃው አስቸጋሪ ጉዞ መሆኑን አውቀዋል ። ከሁሉም በላይ ደግሞ አብዮታዊ ወጣቶች ለዚህ የተወሳሰበ ትግል የሚጠበቅባቸውን መስዋዕትነት እየተቀበሉ ከኢትዮጵያ ጭቁኖች ጎን ለመሰለፍ ብቁና ዝግጁ መሆናቸውን አሳይተዋል ። የመዋሃድ ዘመቻቸውን ለመበተን ይፍጨረጨሩ የነበሩ ኃይሎች ሁሉ ዞሮ ዞሮ ፀረ— ሕዝብና ፀረ— አብዮት ኃይሎች ናቸውና አሁንም ከፊት ለፊትም ሆነ በስተጀርባ እየመጡ ገና ለረዥም ጊዜ እንደሚፈታተኗቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል ።

እነዚህ ፀረ— ሕዝብ ኃይሎች አብዮቱን እንዳይቀለብሱት የኢትዮጵያ ወጣቶች ፀረ— ዘመቻውን ሴራ ባከሸፉበት ታጋይነትና ታታሪነት ይቋቋሟቸዋል ። ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጋርም ከጐናቸው ተሰልፈው ደማቸውን በማፍሰስ ያለመለሙትን የትግል አንድነት ከእንግዲህ ወዲያ ሊሰብረው የሚችል ምንም ዓይነት ኃይል አይኖርም ።

ዛሬ የአብዮታዊ ዘማቾችን ድል እያወሳን የወደፊቱን የጋራ ትግል ጐዳና በምንተልምበት በዚች ታሪካዊ ወቅት እስከዛሬ ድረስ በዚህ ትግል ለጋ ሕይወታቸውን ሳይሳሱ ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ነፃነት አሳልፈው የሰጡትን ዘማች ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን፤ አዝማች መለዮ ለባሾችንና መምህራንን በሙሉ ከልብ እናስታውሳቸዋለን ። በነዚህ ወገኖቻችን ንጹህ ደም የሚያስተጋባውን የትግል ጥሪ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ሰምተው እነሱ ለወደቁለት የነፃነት ተጋድሎ ተነስተዋልና « በግፍ ተጨፈጨፋችሁ እንጂ በከንቱ አልሞታችሁም » እንላቸዋለን ። እኛ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ከቆራጥነታቸው አርአያነትን ወስደናልና ከትግላቸው ትምህርት ቀስመናልና የነፃነቱ ትግል ይቀጥላል ።

በዚህ ትግል የምንገነባት አዲሲቱ ኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ታሪኳን የጻፈችው በነዚህ ታጋይ ወገኖቻችን ንጹህ ደምም መሆኑን ስለምናውቅ ድላችንን ላለማስደፈርም ሆነ አዳዲስ ድሎችን እየተጐናጸፍን ወደፊት ለመጓዝ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከመቸውም ይበልጥ ብቁና ዝግጁ መሆናችንን ጠላቶቻችን ሁሉ ሊያውቁት ይገባቸዋል ።